የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮<br>አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 16[th] Year No. 46<br>ADDIS ABABA 11[th] August, 2010 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ ዓ.ም


የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ...... ገጽ ፭ሺ፬፻፴፪


አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪

## ስለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ የወጣ አዋጅ

በሰው ሀይወትና ንብረት ላይ በመድረስ ላይ ላለው የመንገድ ትራፊክ አደጋ አንዱ መንስኤ የተሽከርካሪ ምዝገባና ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ስርዓት ችግር ያለው ሆኖ በመገኘቱ በመሆኑ፤

የተሽከርካሪ ምዝገባና ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያስችል ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መመዘኛ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 16.00

CONTENTS

Proclamation No. 681/2010


Vehicles Identification, Inspection and Registration Proclamation ...Page 5432


PROCLAMATION NO. 681/2010

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE IDENTIFICATION, INSPECTION AND REGISTRATION OF VEHICLES

**WHEREAS,** the prevailing occurrence of traffic accident against humanity and property arise, among other factors, due to the deficiency of vehicles registration and annual inspection procedure;

**WHEREAS,** it has become necessary to set internationally acceptable standard to implement uniform vehicles registration and annual inspection procedure at the national level;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Vehicles Identification, Inspection and Registration Proclamation No.681/2010."


Scanned by CamScanner

፲/ "የመለያ ቁጥር ሠሌዳ" ማለት ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል በተሽከርካሪው ላይ የሚደረግ መለያ ቁጥሮች የተጻፈበት ሠሌዳ ነው፤

10/ "identification number plate" means a plate upon which the identification number of a particular vehicle is printed and which is affixed to the vehicle for easy identification on the road;

፲፩/ "የኢንተርናሽናል ትራፊክ" ማለት በውጭ አገር የተመዘገበና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንገዶች ላይ ለተወሰነ ጊዜ ለመሽከርከር እውቅና የተሰጠው ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ እውቅና የሚሰጠው ተሽከርካሪው የተመዘገበበት አገር በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ የተመዘገበ ተሽከርካሪ በመንገዶቹ ላይ እንዲሽከረከር የሚፈቅድ ከሆነ ነው፤

11/ "international traffic" means a vehicle registered in a foreign country recognized to operate on the road of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; provided however, that such recognition shall be effected on the basis of reciprocity;

፲፪/ "የአካል ጉዳተኛ ጋሪ" ማለት ባለመንኮራኩር ወንበርና ባለሦስት እግር ብስክሌት የመሳሰለ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን ለማጓጓዝ ብቻ የተሰራና ለዚህ ሥራ ብቻ የሚውል ተሽከርካሪ ነው፤

12/ "carriage of handicap" means any vehicle designed and used solely for the transport of handicap persons such as wheel chair and tricycle;

፲፫/ "በመዝገብ የተያዘ ተሽከርካሪ" ማለት በባለፋብሪካ፣ በነጋዴ፣ በዳግም ሰሪ ወይም ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን በሚሰበስብ ሰው መዝገብ ለሽያጭ የተያዘ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤

13/ "inventory vehicle" means any vehicle which is part of the stock of any manufacturer, dealer, re-builder or wrecker kept for sale;

፲፬/ "ባለፋብሪካ" ማለት ተሽከርካሪዎችን ሠርቶ ወይም ገጣጥሞ በማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

14/ "manufacturer" means any person engaged in the business of manufacturing or assembling vehicles;

፲፭/ "የመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ" ማለት የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ሆኖ ለወታደራዊ ተግባር ብቻ እንዲውል የተመደበ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤

15/ "defense force vehicle" means any vehicle owned by the Ministry of National Defense that is used strictly for military purposes;

፲፮/ "ኦፊሲዬል ሰነዶች" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለንብረትነትን በሚገባ ለማሳወቅና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች፣ የጉምሩክ ሰነዶች፣ የቴክኒክ ምርመራ ቅጾች፣ ደብዳቤዎችና ሌሎች ጽሁፎች ናቸው፤

16/ "official records" means all applications, customs documents, technical inspection forms, pieces of correspondence and other documents required pursuant to this Proclamation for proper title certification and annual inspection;

፲፯/ "ኦፊሲዬል መዝገብ" ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረትነትንና ዓመታዊ ምርመራን የሚመለከቱ መግለጫዎች የሚጻፉበት መዝገብ ነው፤

17/ "official register" means the registry in which all particulars of title certification of vehicles and annual inspections are entered;

Scanned by CamScanner

፲፰/ "ባለይዞታ" ማለት የባለንብረት መብት ባይኖረውም አንድ ተሽከርካሪ ይዞ ለመጠቀም ሕጋዊ መብት ያለው ማናቸውም ሰው ነው።

፲፱/ "ዳግም ሰሪ" ማለት ማንኛውንም አሮጌ ወይም አዲስ ተሽከርካሪ ዋና ዋና ዕቃዎቹን በማውለቅ፣ በመለወጥ ወይም በመጨመር በመጀመሪያ አሰራሩ ላይ ዓይነተኛ ለውጥ አድርጎ የማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።

፳/ "የመመርመሪያ ጊዜ" ማለት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ የሚከናወንበት ጊዜ ነው።

፳፩/ "ሬከር" ማለት ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን በመፈታታት ጠቃሚ ክፍሎቻቸውን ለዳግም አገልግሎት የማቅረብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።

፳፪/ "የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር" ማለት አግባብነት ባለው አካል ለአንድ ተሽከርካሪ ባለንብረት የሚሰጥ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው።

፳፫/ "ጊዜያዊ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ" ማለት አንድ ተሽከርካሪ ምዝገባን እስከሚያካሂድ ድረስ ለቅድመ ምዝገባ ዝግጅት አግባብነት ባለው አካል የሚሰጥ ጊዜያዊ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ነው።

፳፬/ "ነጋዴ" ማለት ተሽከርካሪ በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።

፳፭/ "የተሽከርካሪ ምርመራ" ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑንና መንቀሳቀስ የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው።

፳፮/ "ባለሥልጣን" ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው።

፳፯/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት ባለሥልጣኑ ወይም ተሽከርካሪ ለመመዝገብና ለመመርመር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው።

18/ "possessor" means any person having the right to enjoy the immediate use and control of a vehicle, without necessarily having the full rights of ownership;

19/ "re-builder" means any person engaged in the business of materially altering vehicles from their original construction by the removal, alternation or addition of essential parts, whether new or used;

20/ "inspection period" means the annual period of inspection conducted for vehicles;

21/ "wrecker" means any person engaged in the business of scrapping vehicles and salvaging their reusable parts;

22/ "title certificate book" means declaration of ownership issued by the appropriate organ to the owner of a vehicle;

23/ "temporary operating permit" means transitional permit issued by the appropriate organ for the preparation of registration;

24/ "dealer" means any person who engages in the business of buying and selling of vehicles;

25/ "vehicle inspection" means technical inspection conducted to ensure that a vehicle is technically worthy of being driven on the road;

26/ "Authority" means the Transport Authority established under the Transport Proclamation No. 468/2005;

27/ "appropriate organ" means the Authority or a regional state organ empowered to register and inspect vehicles;

Scanned by CamScanner

፳፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚሽከረከሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለ ምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር</u>

### ፬. <u>ምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ስለማስፈለጉ</u>

የማንኛውም ተሽከርካሪ ባለንብረት ተሽከርካሪውን በማንኛውም መንገድ ላይ ለማንቀሳቀስ ምዝገባ በማካሄድ አግባብነት ካለው አካል የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መቀበል አለበት።

### ፭. <u>ምዝገባና የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የሚያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች</u>

የሚከተሉት ተሽከርካሪዎች የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርና ምዝገባ አያስፈልጋቸውም፦

፩/ በመዝገብ የተያዙ ተሽከርካሪዎች፤

፪/ በኢንተርናሽናል ትራፊክ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፤

፫/ ከፍተኛ ፍጥነታቸው በሰዓት ከ፳ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፤

፬/ የአካል ጉዳተኛ ጋሪዎች።

### ፮. <u>ለምዝገባና ለባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩/ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪን በሚመለከት አግባብነት ላለው አካል የሚቀርብ የምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ማመልከቻ ከተሽከርካሪው የጉምሩክ ዲክሌራሲዮንና ከሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

28/ "person" means a natural or juridical person;

29/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply to vehicles operating on Ethiopian roads.

## <u>PART TWO</u>
## <u>REGISTRATION AND TITLE CERTIFICATION</u>

### 4. <u>Requirement of Registration and Title Certificate Book</u>

The owner of any vehicle upon registration shall obtain a title certificate book for the vehicle from the appropriate organ in order to operate the said vehicle on any road.

### 5. <u>Exemptions from Registration and Title Certificate Book</u>

The following vehicles shall be exempted from the requirement of registration and obtaining title certificate book:

1/ inventory vehicles;

2/ vehicles engaged in international traffic;

3/ special mobile equipment with a maximum speed of less than 20 km per hour;

4/ carriages of handicaps.

### 6. <u>Application for Registration and Title Certificate Book</u>

1/ Any application to be submitted to the appropriate organ for registration and title certificate book relating to an imported vehicle shall be accompanied with customs declaration of the vehicle and other necessary documents.

Scanned by CamScanner

፪/ አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ተሽከርካሪን እንደመዘገበ ለአመልካቹ የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ይሰጠዋል።

## ፰. ስለምዝገባ ለውጥና የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርን ስለማሳረምና ስለመተካት

፩/ በኦፊስዮል መዝገብ ውስጥ ወይም በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ላይ ከሰፈሩት መግለጫዎች መካከል የተሳሳተ ነገር መኖሩን ባለቤቱ ሰነዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ስሀተቱን አግባብነት ላለው አካል ማሳወቅና ደብተሩን ለእርምት ማቅረብ አለበት። ይህም ሲሆን ስሀተቱ ያጋጠመው አግባብነት ባለው አካል ጥፋት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ባለንብረቱ ይፈጽማል።

፪/ በኦፊስዮል መዝገቡ ውስጥና በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ ላይ በሰፈሩት መግለጫዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም ምዝገባው እንዲስተካከልና ደብተሩ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል ባለቤቱ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ደብተሩን ማቅረብ አለበት። ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያም ይፈጽማል።

፫/ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ ባለቤቱ ምትክ ደብተር እንዲሰጠው ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማመልከት አለበት።

፬/ አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ በጠፋው ምትክ ደብተር ይሰጠዋል።

፭/ ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰረዝና እንዲወገድ ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት።

## ፱. የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርን ስለመመለስ

ማንኛውም ተሽከርካሪ ከአገር እንዲወጣ ወይም እንዲወላለቅ ወይም ጨርሶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀስ በተደረገ በ፴ ቀናት ውስጥ ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ እንዲሰረዝ አግባብነት ላለው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት።

2/ The appropriate organ shall, upon registration of a vehicle under sub-article (1) of this Article, issue the applicant with a title certificate book thereof.

## 8. Change of Registration and Correction and Replacement of Title Certificate Book

1/ Where the holder of a title certificate book becomes aware of an error in the particulars entered in the official register or the title certificate book, he shall notify with in 30 days from the date of issuance of the same to the appropriate organ and present the book for correction. In such case, he shall be required to pay the prescribed fees unless the error was totally attributable to the fault of the appropriate organ.

2/ Where a change of fact occur in the particulars entered in the official register or the title certificate book, the holder thereof shall, within 30 days notify the appropriate organ and present the book for the amendment of the register and the book accordingly, upon payment of the prescribed fee.

3/ Where a title certificate book is lost, damaged or becomes illegible, the holder thereof shall promptly submit an application to the appropriate organ for a replacement.

4/ The appropriate organ shall, upon receipt of an application in accordance with sub-article (3) of this Proclamation and payment of the prescribed fees, issue to the applicant a replacement title certificate book.

5/ A person who has recovered a title certificate book for which a replacement has been issued shall promptly surrender the extra title certificate book to the appropriate organ for cancellation and destruction.

## 9. Surrender of Title Certificate Book

Where any vehicle has been exported, scrapped or permanently removed from use on the roads, the owner or possessor thereof shall, within 30 days, surrender the title certificate book to the appropriate organ for its cancellation.

Scanned by CamScanner

## ክፍል ሦስት
## ስለመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች
## ንዑስ ክፍል አንድ
## የወል ድንጋጌዎች

**፲. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ አስፈላጊነት**

ማናቸውም ተሽከርካሪ አግባብነት ባለው አካል የተሰጠ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ካልተለጠፈለት በስተቀር በማንኛውም መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ ሊደረግ አይችልም።

**፲፩. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች**

የሚከተሉትን ተሽከርካሪዎች በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

፩/ በኢንተርናሽናል ትራፊክ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፤

፪/ ከፍተኛ ፍጥነታቸው በሰዓት ከ፳ ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፤

፫/ የአካል ጉዳተኛ ጋሪዎች።

**፲፪. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ እንዲታይ ስለማድረግ**

፩/ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በሚከተለው አኳኋን ተለጥፎ እንዲታይ መደረግ አለበት፡-

ሀ/ ለሞተር ብስክሌት ሲሆን፤ በሞተር ብስክሌቱ የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን፤

ለ/ ለባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን በተሽከርካሪው የፊትና የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን፤

ሐ/ ለተሣቢ ሲሆን በተሳቢው የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን።

፪/ የማንኛውም ተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጎልቶ እንዲታይና ከዕይታ እንዳይ ከለል መደረግ አለበት።

## PART THREE
## IDENTIFICATION NUMBER PLATES
## SECTION ONE
## COMMON PROVISIONS

**10. Requirement of Identification Number Plate**

Any vehicle may not be operated on any road unless an identification number plate issued by the appropriate organ has been affixed to it.

**11. Exemptions from Identification Number Plate**

The provisions of Article 10 of this Proclamation shall not be applicable with respect to the following vehicles:

1/ vehicles engaged in international traffic;

2/ special mobile equipment with maximum speed of less than 20 km per hour;

3/ carriages of handicaps.

**12 Display of Identification Number Plates**

1/ Identification number plates shall be affixed and displayed as follows:

a) in case of a motor cycle, at the right angle to the longitudinal axis of the back of the motor cycle;

b) in case of a motor vehicle, at the right angles to the longitudinal axis of both the front and back elevations of the vehicle arranged for such purpose;

c) in case of a trailer, at the right angle to the longitudinal axis of the back of the trailer arranged for such purpose.

2/ An identification number plate of any vehicle shall be displayed so as to be clearly distinguishable and be free from any obstruction.

Scanned by CamScanner

## ፲፫. የመለያ ቁጥር ሰሌዳን ስለመለወጥና ስለመተካት

፩/ የመለያ ቁጥር ሰሌዳን የቀለም ኅብር፣ የፊደል ጥምረት ወይም ማናቸውም ሌላ ምልክት በተመለከተ ግድፈት መኖሩን የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ሠሌዳው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ውስጥ የመለያ ቁጥር ሰሌዳው በትክክለኛው ሰሌዳ እንዲለወጥ አግባብነት ላለው አካል ማቅረብ አለበት። ይህም ሲሆን ግድፈቱ ያጋጠመው አግባብነት ባለው አካል ጥፋት ምክንያትነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው ይፈጽማል።

፪/ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ምትክ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ እንዲሰጠው ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማመልከት አለበት።

፫/ አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ ምትክ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ይሰጠዋል።

፬/ ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን የመለያ ቁጥር ሰሌዳ መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው ሰሌዳ እንዲወገድ አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት።

## 13. Exchange and Replacement of Identification Number Plates

1/ Where the owner or possessor of a vehicle becomes aware of a defect in the color or letter combination or any other feature of an identification number plate, he shall, within 10 days starting from the date of issuance of the same present the plate to the appropriate organ for exchange with the correct plate. In such case, he shall be required to pay the prescribed fees unless the defect was totally attributable to the fault of the appropriate organ.

2/ Where an identification number plate is lost, damaged or becomes illegible, the owner or possessor of the vehicle shall promptly submit an application to the appropriate organ for a replacement.

3/ The appropriate organ shall, upon receipt of an application pursuant to sub-article (2) of this Article and payment of the prescribed fees, issue to the applicant a replacement identification number plate.

4/ A person who has recovered an identify-ication number plate for, which a replacement has been issued shall promptly surrender the extra plate to the appropriate organ for destruction.

## ፲፬. ስለመለያ ቁጥር ሰሌዳ አለመኖር

፩/ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አለመኖር የተሽከርካሪው ባለንብረትነት በሚገባ ያልተረጋገጠ ለመሆኑ መነሻ ግምት ያስወስዳል። የተሽከርካሪውን ባለንብረ-ትነት በሚገባ የማረጋገጥ ተግባርም የተሽከርካሪው ባለይዞታ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም ተሽከርካሪ ትክክለኛ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ሳይደረግበት በማንኛውም መንገድ ላይ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ የባለንብረትነቱ ሁኔታ በሚገባ እስኪጣራ ድረስ አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን ይዞ ማቆየት ይችላል።

## 14. Absence of Identification Number Plates

1/ The absence of a vehicle's identification number plate shall be regarded as prima facie evidence that the vehicle has not had its title properly certified. The onus of proving that the title of the vehicle in question has been properly certified shall rest with the possessor of the said vehicle.

2/ Where a vehicle being operated on any road does not bear proper identification number plates, the appropriate law enforcement body shall have the power to detain such vehicle until the facts of ownership are properly certified.

Scanned by CamScanner

**፲፭. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች**

፩/ አግባብነት ባለው አካል የሚሰጡ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ይዘት፣ ቅርጽ እና ሚስጥራዊ ምልክቶች በባለሥልጣኑ ይወሰናሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች

**፲፮. ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ስለመስጠት**

አግባብነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/፣ /፪/ ወይም /፫/ መሠረት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ተመሥርቶ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር በሚሰጥበት ወቅት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተሽከርካሪው የሚያስፈልገውን ያህል ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች መስጠት አለበት፡፡

**፲፯. ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

ማንኛውም ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ መሠረት እንዲለወጥ ወይም እንዲተካ ካልተደረገ በስተቀር ተሽከርካሪው እንዲወላልቅ ወይም ጨርሶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀስ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፡፡

**፲፰. ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎችን ስለመመለስ**

ማንኛውም ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ የተመለከተው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ ወይም የተሽከርካሪው ምዝገባ ሲሰረዝ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ከሚመለሰው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

**15. Types and Symbols of Identification Number Plates**

1/ The types and symbols of identification number plates to be issued by the appropriate organ shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the content, form, size and security features of identification number plates shall be determined by the Authority.

## SECTION TWO
## PERMANENT IDENTIFICATION NUMBER PLATES

**16. Issuance of Permanent Identification Number Plates**

Where the appropriate organ issues a title certificate book on the basis of an application submitted pursuant to sub-article (1), (2) or (3) of Article 6 of this Proclamation, it shall, upon payment of the prescribed fees, issue the required quantities of permanent identification number plates with respect to the vehicle in question.

**17. Validity of Permanent Identification Number Plates**

Any permanent identification number plate shall, unless exchanged or replaced pursuant to Article 13 of this Proclamation, remain valid until the vehicle has been scrapped or permanently removed from use on the road.

**18. Surrender of Permanent Identification Number Plates**

Where the validity period of any identification number plate expires as provided for in Article 17 of this Proclamation, the owner or possessor of the vehicle shall surrender the plate to the appropriate organ together with the title certificate book to be surrendered in accordance with Article 9 of this Proclamation.

Scanned by CamScanner

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች

### ፲፱. ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ስለመስጠት

ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ከባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር መስጠት የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ከመሰጠቱ በፊት ተሽከርካሪውን በማንኛውም መንገድ ላይ ለማንቀሳቀስ የሚያስገድድ ምክንያት ሲኖር አግባብነት ያለው አካል ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተሽከርካሪው የሚያስፈልገውን ያህል ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ከጊዜያዊ ማንቀሳቀሻ ፈቃድ ጋር መስጠት ይችላል።

### ፳. ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ

፩/ ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ፲፭ ቀናት ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ ለ፲፭ ቀናት ሁለት ጊዜ እንዲራዘም አግባብነት ያለው አካል ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ የዕለት መለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ወይም ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ለተሽከርካሪው ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ከተሰጠ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ሰሌዳውን አግባብነት ላለው አካል ወዲያውኑ ማስረከብ አለበት።

## ንዑስ ክፍል አራት
## ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች

### ፳፩. የተላላፊ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አጠቃቀል

፩/ ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የሚያገለግለው በተሽከርካሪ ባለፋብሪካ፣ ነጋዴ ወይም ዳግም ሠሪ መዝገብ ለተያዙ ተሽከርካሪዎች ብቻ በማለዋወጥ እንዲሰራበት ነው።

## SECTION THREE
## TEMPORARY IDENTIFICATION NUMBER PLATES

### 19. Issuance of Temporary Identification Number Plates

Where it becomes impossible to issue a permanent identification number plate simultaneously with a title certificate book in accordance with Article 16 of this Proclamation or where there is a compelling reason to operate a vehicle on any road prior to the issuance of a title certificate book, the appropriate organ may, upon payment of the prescribed fees, issue the required quantities of temporary identification number plates and temporary operating permit with respect to the vehicle in question.

### 20. Validity Period of Temporary Identification Number Plates

1/ A temporary identification number plate shall be valid for a period of 15 days from the date of issuance.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article the validity period of temporary identification number plate may, upon payment of the prescribed fees, be extended twice by the appropriate organ for additional 15 days each.

3/ Where the validity period of a temporary identification number plate expires or a permanent identification number plate is issued within its validity period, the owner or possessor of the vehicle shall immediately return the plate to the appropriate organ.

## SECTION FOUR
## TRANSFERABLE IDENTIFICATION NUMBER PLATES

### 21. Use of Transferable Identification Number Plate

1/ A transferable identification number plate may be used interchangeably among inventory vehicles belonging to a manufacturer, dealer or re-builder of vehicles.

Scanned by CamScanner

፪/ ተላላፊ ሰሌዳ የተደረገበት ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ለሚከተሉት ጉዳዮች ብቻ ነው፡-

ሀ/ ከገባበት ወደብ ወይም ከተገዛበት ሥፍራ ወደ ንግድ ሥፍራ ለማዛወር፤

ለ/ አልፎ አልፎ ከመጋዘን ወደ ማሳያ ክፍል ወይም ለሽያጭ ወደ ሚቀር- ብበት ሥፍራ ለመውሰድና ወደ መጋ- ዘን ለመመለስ፤

ሐ/ ለፍተሻ ወይም ለማሳያ ከሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ለማይበልጥ የደርሶ መልስ ርቀት ለሚደረግ መንዳት፤

መ/ ከንግድ ሥፍራ ለገዥ ወይም ለተላለፈለት ሌላ ሰው ወደማስረከቢያ ስፍራ ለማድረስ፤ ወይም

ሠ/ ወደ ምርመራና ምዝገባ ቦታ ለማድረስ።

፫/ የተሽከርካሪ ባለፋብሪካ፣ ነጋዴ ወይም ዳግም ሰሪ መገልገያ በሆኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ምንጊዜም ቢሆን ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ አይደረግም።

**፳፪. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ስለመስጠት**

፩/ ማናቸውም የተሽከርካሪ ባለፋብሪካ፣ ነጋዴ ወይም ዳግም ሰሪ ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች እንዲሰጡት ሲፈልግ ማመልከቻውን በተባለው ሥራ ላይ እንዲሰማራ ከተሰጠው ፈቃድ ቅጅ ጋር አያይዞ አግባብነት ላለው አካል ማቅረብ አለበት።

፪/ አግባብነት ያለው አካል የቀረበለት ማመልከቻና የተያያዘው የፈቃድ ቅጅ እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ የተጠየቁትን ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ለአመልካቹ ይሰጠዋል።

**፳፫. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

፩/ ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት ብቻ ነው።

2/ A vehicle displaying a transferable identification number plate may be operated on any road for the following purposes only:

a) transfer from port of entry or place of acquisition to place of business;

b) occasional transfer from storage area to a showroom or retail display area, and vise versa;

c) testing or demonstration drive of a total round trip distance not exceeding 25 kilometers;

d) transfer form place of business to place of delivery to a buyer or other transferee; or

e) transfer to inspection and registration place.

3/ Transferable identification number plates may never be used in connection with service vehicles of a manufacturer, dealer or re-builder of vehicles.

**22. Issuance of Transferable Identification Number Plates**

1/ Any vehicle manufacturer, dealer or re-builder seeking transferable identification number plates shall submit his application to the appropriate organ together with a copy of his license authorizing him to engage in such business.

2/ The appropriate organ shall, upon being satisfied as to the genuineness and regularity of the application submitted as well as the accompanying copy of license and upon payment of the prescribed fees, issue the requested transferable identification number plates to the applicant.

**23. Validity Period of Transferable Identification Number Plates**

1/ A transferable identification number plate shall be valid for one year from the date of issuance.

Scanned by CamScanner

**፳፯.ተሽከርካሪዎችን ለምርመራ ስለማቅረብ**

፩/ የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ተሽከርካሪውን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ማቅረብ አለበት።

፪/ ማንኛውም አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ተሽከርካሪውን በመመርመሪያ ጊዜ ለምርመራ ማቅረብ የማያስችለው በቂ ምክንያት ሲያጋጥመው አግባብነት ያለው አካል ለምርመራ የማቅረቢያ ጊዜውን ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝምለት ይችላል።

**፳፰.የምርመራ ጣቢያዎች**

፩/ አግባብነት ባለው አካል የተቋቋመ የምርመራ ጣቢያ ወይም አግባብነት ባለው አካል ውክልና የተሰጠው ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ በተደነገገው የምርመራ መሥፈርቶች መሠረት የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ ማካሄድ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ውክልና የተሰጠው ድርጅት የምርመራ መሥፈርቶችን በሚገባ ተከትሎ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ እንዲካሄድ ካላደረገ አግባብነት ካለው አካል ጋር በገባው የውክልና ስምምነት መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

**፳፱. ስለምርመራ መሥፈርቶች**

፩/ በምርመራ ጣቢያዎች ምርመራ ለማካሄድ ሥልጣን የተሰጠው መርማሪ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ተሽከርካሪ መመርመር አለበት፡-

ሀ/ ተሽከርካሪውን ለመለየት በአካሉ፣ በሻንሲው ወይም በሞተሩ ላይ በፋብሪካው የተጻፉትና በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ መግለጫዎች ወይም በመዝገብ ላይ የተጠቀሱት ቁጥሮችና ፊደሎች ትክክለኛ መሆናቸውን፣

ለ/ ተሽከርካሪው ለተመዘገበበት ዓላማ አደጋን በማያስከትል አኳኋን በመንገድ ላይ ሊንቀሳቀስ የሚችል መሆኑን፣

**27. Presentation of Vehicles for Inspection**

1/ The owner or possessor of a vehicle shall present the vehicle for annual inspection in accordance with the provisions of this Proclamation,.

2/ The appropriate organ may extend the period of inspection for not more than two months in case of a sufficient cause that prevent an applicant to present his vehicle for inspection in accordance with sub-article (1) of this article within the inspection period.

**28. Inspection Stations**

1/ An inspection station established by the appropriate organ or an organization delegated by the appropriate organ shall undertake annual inspection of vehicles in accordance with the inspection criteria provided for in Article 29 of this Proclamation.

2/ Any organization delegated pursuant to sub-article (1) of this Article shall be liable in accordance with the contract of agency concluded with the appropriate organ for not ensuring strict observance of the inspection criteria in undertaking annual inspection of vehicles.

**29. Inspection Criteria**

1/ An authorized inspector of an inspection station shall inspect each vehicle presented for the purpose of establishing:

a) the authenticity of the numbers and letters placed on the body, chassis or engine of the vehicle by the manufacturer and which are included in the particulars of its title certificate book or official register for the purpose of identifying the vehicle,

b) the vehicle's road worthiness in performing, in a safe manner, the purposes for which it is registered,

Scanned by CamScanner

፪/ በዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ላይ በሰፈሩት መግለጫዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም ተለጣፊ ምልክቱ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በአስር ቀናት ውስጥ ተለጣፊ ምልክቱን አግባብ ላለው አካል ማቅረብ አለበት። ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያም ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው ይፈጽማል።

፫/ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ምትክ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ወዲያውኑ አግባብ ላለው አካል ማመልከት አለበት።

፬/ አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ካደረገ በኋላ ምትክ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል።

፭/ ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰረዝና እንዲወገድ ወዲያውኑ አግባብ ላለው አካል ማስረከብ አለበት።

## ፴፭. ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ

ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለተለጣፊ ምልክቱ መስጠት መሠረት የሆነው የምርመራ ምስክር ወረቀት ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

## ፴፮. ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት አለመኖር

፩/ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አለማድረጉን መነሻ ግምት ያስወስዳል። ተሽከርካሪው መመርመሩን የማስረዳቱ ተግባርም የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም የባለይዞታ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም ተሽከርካሪ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፫ በመተላለፍ በማንኛውም መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ ከተደረገ የመመርመሩ ሁኔታ በሚገባ እስኪጣራ ድረስ አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን ይዞ ማቆየት ይችላል።

2/ Where a change of fact occur in the particulars of an annual inspection sticker, the owner or possessor of the vehicle shall, within 10 days, present the sticker to the appropriate organ for its amendment accordingly, upon payment of the prescribed fees.

3/ Where an annual inspection sticker is lost, damaged or becomes illegible, the owner or possessor of the vehicle shall promptly submit an application to the appropriate organ for a replacement.

4/ Where an application is submitted to the appropriate organ in accordance with sub-article (3) of this Article, it shall, upon payment of the prescribed fees, issue to the applicant a replacement annual inspection sticker.

5/ A person who has recovered an annual inspection sticker for which a replacement has been issued shall promptly surrender the extra annual inspection sticker to the appropriate organ for cancellation and destruction.

## 35. Validity Period of Annual Inspection Sticker

The validity period of an annual inspection sticker shall be the same as that of the inspection certificate on the basis of which it is issued.

## 36. Absence of Annual Inspection Sticker

1/ The absence of a vehicle's annual inspection sticker shall be regarded as prima facie evidence that the vehicle has not been inspected. The onus of proving that the vehicle in question has been inspected shall rest with the owner or possessor of the said vehicle.

2/ Where a vehicle is operated on any road in violation of Article 33 of this Proclamation the appropriate law enforcement body shall have the power to detain the said vehicle until the facts of registration is properly certified.

Scanned by CamScanner

**፴፯. ስለልዩ ምርመራ**

፩/ ማንኛውም ተሽከርካሪ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴ ድንጋጌ የሚያሟላ ቢሆንም አግባብነት ያለው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ልዩ ምርመራ ሊያደርግበት ይችላል።

፪/ ማንኛውም ተሽከርካሪ፦

ሀ/ በመንገድ ላይ ለማገልገል ብቁ አለመሆኑ፣

ለ/ አሰራሩ፣ መሣሪያዎቹ፣ መጠኑ ወይም ክብደቱ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተወሰኑትን ደረጃዎች የማያሟላ መሆኑ፣ ወይም

ሐ/ በአደጋ ምክንያት ከባድ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ፣

በግልጽ የሚታይ ሲሆን አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለሚደረግ ልዩ ምርመራ እንዲቀርብ ሊያስገድድ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚደረግ የተሽከርካሪ ልዩ ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም።

**ክፍል አምስት**
**ስለተሽከርካሪዎች ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች**

**፴፰. ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች ስለመያዝ**

አግባብነት ያለው አካል ባለንብረትነታቸው የታወቀና የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን በሚ-መለከት ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች እንዲ-ሁም የዓመቱን የተጠቃለለ የተሽከርካሪዎች ዝርዝር አደራጅቶ በሚገባ ይይዛል።

**፴፱. የተሰረቁ ወይም የተለወጡ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር**

፩/ አግባብነት ያለው አካል የተሰረቁ፣ የተለወጡ፣ ጠፍተው የተገኙና ባለንብረቱ ያልተገኘ ተሽከርካሪዎችን የተጠቃለለ ዝርዝር አደራጅቶ በሚገባ ይይዛል፣ ሲጠየቅም ለሚመለከተው አካል ይሰጣል።

**37. Special Inspection**

1/ The appropriate organ may, where it finds it necessary, conduct a special inspection of a vehicle irrespective of the fact that the requirements of Article 30 of this Proclamation is complied with.

2/ The appropriate law enforcement body may require the presentation of a vehicle for a special inspection to be conducted in accordance with sub-article (1) of this Article where the vehicle is obviously:-

a) not in a road worthy condition;

b) not in compliance with the standards, set in accordance with the law, relating to its construction, equipment, size or weight; or

c) damaged to a substantial degree due to an accident.

3/ No fee shall be charged for special inspection conducted pursuant to this Article.

**PART FIVE**
**OFFICIAL REGISTER AND RECORDS OF VEHICLES**

**38. Maintenance of Official Register and Records**

The appropriate organ shall properly maintain official register and records of vehicles that have been certified and registered as well as their cumulative list of the current year.

**39. List of Stolen or Converted Vehicles**

1/ The appropriate organ shall keep and properly maintain a cumulative list of stolen, converted, recovered and unclaimed vehicles reported to it; and upon request, distribute the list to the appropriate bodies.

Scanned by CamScanner

፫/ ለተሽከርካሪው በፋብሪካው ከተገጠመለት መደበኛ መብራት ውጪ ተጨማሪ መብራት ማስገባት፣

፬/ የነጂውን የማየት ችሎታ በሚያውክ ሁኔታ አሻንጉሊቶችን ወይም ሌሎች ጌጣጌጦችን ማስቀመጥ፣ ወይም

፭/ አግባብነት ካለው አካል አስቀድሞ ሳያስ ፈቅድ በባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን በተሽከርካሪው አካላት ላይ መቀየር ወይም ተሽከርካሪ ውን መበተን፣

አይችልም።

## ፵፫. የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

አግባብነት ያለው አካል እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ አንፀባራቂ የሆኑ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች እንዲደረጉ ሊያዝ ይችላል።

## ፵፬. ስለሰሌዳ ሥራ እና ቁጥር አፃፃፍ

ባለሥልጣኑ ሰሌዳ አምርቶ የማሰራጨት ተግባሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ፊደላትና ቁጥሮች ያለው ሰሌዳ በሥራ ላይ ማዋል ይችላል።

## ፵፭. ስለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች

፩/ ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች የባለቤ- ትነት መታወቂያ ደብተር፣ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎችና ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት የሚሰጠው በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል።

፪/ ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች የሚሰ- ጠው የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተመለከቱት የቀለም ሕብር፣ የፊደል ጣምራና ምልክቶች የተለየ መሆን አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ አዋጅ እንደአግባብነቱ ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

3/ fix his vehicle with extra lights other than the ordinary lights affixed by the manufacturer;

4/ keep dolls or other decorative objects in a manner that obstructs the vision of the driver; or

5/ alter on the body of his vehicle any information included in the particulars of the title certificate book or scrap the vehicle, without prior authorization of the appropriate organ.

## 43. Warning Signs

The appropriate organ may, whenever it deems it necessary, order the affixation of reflective warning signs on a vehicle.

## 44. Manufacturing and Digits of Plates

The Authority may, without prejudice to its duty to manufacture and distribute plates, introduce additional configuration of alphabets and numbers of plates when it is deemed necessary.

## 45. Defense Force Vehicles

1/ Title certificate books, identification number plates and annual inspection stickers of defense force vehicles shall be issued by the Ministry of National Defense.

2/ The color and letter combinations and symbols of identification number plates to be issued with respect to defense force vehicles shall be different from those specified under the Schedule attached hereto.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-articles(1) and (2) of this Article, this Proclamation shall, mutatis mutandis, be applicable with respect to defense force vehicles.

Scanned by CamScanner

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት አግባብነት ባለው አካል በተጣለበት የገንዘብ መቀጮ ቅር የተሰኘ ሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፭/ መቀጮው የተጣለበት ሰው አግባብነት ያለው አካል ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ መሠረት ይግባኝ አቅርቦ ከሆነ ይግባኙ ውድቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ገቢ ሳያደርግ ቢቀር ክፍያው መፈጸሙን የሚያሳይ ደረሰኝ እስኪያቀርብ ድረስ የሚመለከተው ፖሊስ ጥፋቱ የተፈጸመበ-ትን ተሽከርካሪ ይዞ የማቆየት ሥልጣን ይኖረዋል።

## ፵፱. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## ፶. ስለአዋጁ አፈጻጸም

ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና መመሪያ ዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል፤ የመመዝገብና የመመርመር ኃላፊ ነት ለተሰጣቸው የክልል አካላት አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

## ፶፩. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሣቢ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ደንብ ቁጥር ፫፻፷/፲፱፻፷፩ /እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛ-ውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአ-ሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

4/ A person aggrieved with the imposition of fines pursuant to the provisions of sub-article (1) of this Article may lodge an appeal to the competent court within 30 days from the date of the decision of the appropriate organ.

5/ Where a person fails to settle fines imposed on him within 30 days from the date of the decision of the appropriate organ or, in case of appeal pursuant to sub-article (4) of this Article, from the date the appeal is rejected, the concerned police officer shall have the power to detain the vehicle, with respect to which the offense has been committed, until the presentation of a receipt of payment.

## 49. Power to Issue Regulation

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry of Transport and Communication may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

## 50. Implementation of the Proclamation

The Authority shall, with a view to ensuring the uniform application of the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder throughout the country, follow up their implementation and provide the necessary technical assistance to regional organs in charge of registration and inspection of vehicles.

## 51. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Motor Vehicle and Trailer Identification, Inspection and Registration Regulation No. 360/1969 (as amended) is hereby repealed.

2/ No law, regulations, directives or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

Scanned by CamScanner

**፶፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**52. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2010**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned by CamScanner

# SCHEDULE

## TYPES AND SYMBOLS OF IDENTIFICATION NUMBER PLATES OF VEHICLES

| No | Type of Plate | Colour Combination and Code Number/Letter Combination | Meaning |
|---|---|---|---|
| 1 | Taxi Plate | White ground with red letters and numerals and code number "1" in a red circle on the left hand side | To be issued for vehicles engaged in taxi transport service |
| 2 | Private Plate | White ground with dark blue letters and numerals and code number "2" in a blue circle on the left hand side | To be issued for private motor cars used for personal and family purposes |
| 3 | Commercial Plate | White ground with dark green letters and numerals and code number "3" in a green circle on the left hand side | To be issued for vehicles registered for commercial road transport use or car-hire business |
| 4 | Government Plate | White ground with black letters and numerals and code number "4" in a black circle on the left hand side | To be issued for vehicles owned by government agencies |
| 5 | Religious and Civic Societies Plate | White ground with orange letters and numerals and code number "5" in a black circle on the left hand side | To be issued for vehicles owned by the red cross, religious societies, non business associations and similar other institutions |
| 6 | Temporary Plate | White ground with red letters and numerals with the legend "የዕለት" on the left hand side | To be issued for any vehicle for temporary use |
| 7 | Transferable Plate | White ground with light blue letters and numerals with the legend "ተላላፊ" on the left hand side | To be issued for any inventory vehicle owned by a manufacturer, dealer or re-builder for temporary use |
| 8 | Special Mobile Equipment Plate | White ground with red letters and numerals with the legend "ልዩ ተ" on the left hand side | To be issued for any special mobile equipment |
| 9 | Police Plate | Yellow ground with black letters and numerals with the legend "ፖሊስ" on the left hand side | To be issued for vehicles owned by the police |
| 10 | Embassies, International Organizations and Aid Plates | a) White ground with light blue letters and numerals with letter combination "ኮዲ", "የተመ", "CD" and "UN" on yellow stripes on the left and right hand side | a) to be issued for vehicles of "UN" personnel with diplomatic status |

Scanned by CamScanner

| ተ.ቁ | የሰሌዳው ዓይነት | የቀለም ኅብርና መለያ ቁጥር/ የፊደላት ጥምርታ | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| ፲፪ | | "አአ" "AA" | በአዲስ አበባ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፫ | | "አፋ" "AF" | በአፋር ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፬ | | "አማ" "AM" | በአማራ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፭ | | "ቤጉ" "BG" | በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፮ | | "ድሬ" "DR" | በድሬዳዋ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፯ | | "ጋም" "GM" | በጋምቤላ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፰ | | "ሐረ" "HR" | በሐረሪ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፲፱ | | "ኦሮ" "OR" | በኦሮሚያ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፳ | | "ሱማ" "SM" | በሱማሌ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፳፩ | | "ደሕ" "SP" | በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |
| ፳፪ | | "ትግ" "TG" | በትግራይ ክልል የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ያመለክታል |

## ሌሎች ምልክቶች

በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱት የቀለም ኅብርና የፊደል ጣምራዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ የሠሌዳ ዓይነት ሌዘር ኮድ፣ ሆሎግራም እና በቀላሉ የማይታይ ምልክት ይኖረዋል።



Scanned by CamScanner

| No | Type of Plate | Colour Combination and Code Number/Letter Combination | Meaning |
|---|---|---|---|
| 12 | | "አአ" "AA" | Indicate vehicles registered in Addis Ababa |
| 13 | | "አፋ" "AF" | Indicate vehicles registered in Afar State |
| 14 | | "አማ" "AM" | Indicate vehicles registered in Amhara State |
| 15 | | "ቤጉ" "BG" | Indicate vehicles registered in Benshangul Gumuz State |
| 16 | | "ድሬ" "DR" | Indicate vehicles registered in Dire Dawa |
| 17 | | "ጋም" "GM" | Indicate vehicles registered in Gambela State |
| 18 | | "ሐረ" "HR" | Indicate vehicles registered in Harari State |
| 19 | | "ኦሮ" "OR" | Indicate vehicles registered in Oromia State |
| 20 | | "ሱማ" "SM" | Indicate vehicles registered in Somalia State |
| 21 | | "ደሕ" "SP" | Indicate vehicles registered in the State of Southern Nations, Nationalities and Peoples |
| 22 | | "ትግ" "TG" | Indicate vehicles registered in Tigray State |

**Other Features**

Subject to the colour and letter combinations stated in this Proclamation each type of plate shall have laser code, hologram and water marking.

Scanned by CamScanner